እያሲያዙ አገልግሎት እንዲሰጥ እያሳሰብን፣ የተደረገው ማሻሻያ ከ13/08/2014 ጀምሮ ተግባራዊ እንዲሆን በ \\10.12.0.8 ሎካል ሼር አድራሻ ላይ Tariff Classification -Folder/ Tariff Policy and Classification-Folder/ከመስከረም 1.2014 ዓ.ም በኋላ የመጡ የታሪፍ ማሻሻያዎች-Folder/ኮቪድ-19-Folder/ ውስጥ ኮቪድ-19 ታሪፍ ማሻሻያ ሚያዝያ 18 2014 ዓ.ም በሚል የፋይል ስም የተቀመጠ መሆኑን እናሳቃለን።

ከገንዘብ ሚኒስትር ከ13/08/2014 በተላለፈው ዝርዝር ውስጥ የታሪፍ ቁጥራቸው ሳይጠቀስ በጥቅል አገላለጽ የጠቀመጡትን ግብዓቶች በተመለከተ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጤና ሚኒስቴር በዝርዝር በታሪፍ ቁጥር በመለየት ለኮሚሽኑ እስከሚልክ ድረስ አገልግሎት ለመስጠት የምንቸገር መሆኑ ታውቆ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በተቻለ ፍጥነት ዝርዝራቸውን ከነታሪፍ ቁጥራቸው በማዘገጀት ለኮሚሽናችን እንዲያሳውቅ በዚህ ደብዳቤ ግልባጭ እንዲያውቀው ተደርጓል።

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ:-

- ለጤና ሚኒስቴር
- ለገንዘብ ሚኒስቴር

አዲስ አበባ

ግልባጭ:-

- ለጉምሩክ ኦፐሬሽን ዘርፍ
- ለጉምሩክ ኮሚሽን ጽ/ቤት
- ለድህረ እቃ አወጣጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ ስራአመራር ስርአት ፕሮጀክት ጽ/ቤት
- ለንግድ ዕቃ አወጣጥ አሠራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ አቤቱታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት
- ለታሪፍ ፖሊሲ ጥናትና ትንተና ቡድን
- ለታሪፍ ምደባ አሰራርና ድጋፍ ቡድን

ጉምሩክ ኮሚሽን

